በቅድሚያ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ዝግጅት ለአድማጮቹ ሁሉ  እንኳን ለአውሮፓውያን የክርስቶስ ልደት በዓል አደረሳችሁ ለመጭውም 2023 ዓም በሰላምና በጤና ያድርሳችሁ በማለት ምኞቱን ይገልጻል።በማስቀጠልም ሳምንታዊውን  ስርጭታችንን በሳምንታዊው አገር እንዴት ሰነበተች በሚለው የስነጽሁፍ ክፍል ጥንቅራችን  ጀምረን ሌሎቹን ዝግጅቶቻችንን በቅደም ተከተል እናቀርባለን። እንደተለመደው ሙሉ ዝግጅታችንን እንድትከታተሉ በአክብሮት እንጋብዛለን።መልካም ክትትል!

## አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 45

ታህሳስ 16 ቀን 2015ዓም(25-12-2022)

ባሳለፍነው ሳምንት ዝግጅታችን  ሙሉ ትኩረት የሰጠነው ተረኛው የኦሮሙማ ገዢው ቡድን የአዲስ አበባ ከተማን ለመዋጥ መንደርደሪያ ያደረገውን በጫካ  ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው የሥርዓቱ አካል አሸባሪው ኦነግ የሰፋውን  ባንዲራ በግድ  የማውለብለብና የጥላቻ መልእክት ስንኝ የተሸከመ እንጉርጉሮ በግዴታ ለመጫን ያደረገውን ድፍረት በትምህርት ቤቶችና በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች የገጠመውን ተቃውሞ የሚተነትን ነበር።አሁንም በዚሁ ሳምንት ሁኔታው አልተቀዬረም።የተማሪውና የመምህራኑ እንዲሁም የወላጆች ተቃውሞ በመስፋፋት ላይ ሲሆን ሌላውን የማህበረሰብ ክፍል እያካተተ መጥቷል።በዚህ የተደናገጠው የተረኛው ኦሮሙማ አገዛዝም ያለ የሌለ ሃይሉን አሰባስቦ የማጥቃት እርምጃውን ተያይዞታል።ከተማዋ የጦር ቀጠና እስክትመስል ድረስ ከባድ መሣሪያ ባነገቡና በጫኑ  ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ተውጣ ሰንብታለች።በዬትምህርት ቤቱም ውስጥ የሥርዓቱ ጀሮ ጠቢዎችና የጥቃት ሃይሎች ተሰማርተው ተቃውሞውን ያስተባብራሉ  የሚሏቸውን ተማሪዎችና መምህራን በመደብደብና በማፈስ ብዙ ወንጀል እንደፈጸሙባቸው ማስረጃዎች ወጥተዋል።

በዚህ ብቻም ሳይቆም በሥርዓቱ ቁንጮ በአብይ አህመድ ቢሮ ውስጥ የኦሮሙማው ቡድን  ስብሰባ አድርጎ እንዴት እንደፈራለን?27 ዓመት ሙሉ በጥቂቶቹ የወያኔ አገዛዝ ሰጥ ለጥ ብሎ የተገዛ ሕዝብ እንዴት በእኛ በብዙዎቹ አገዛዝ ጊዜ ተቃውሞ ይነሳብናል?የምንፈልገውን ካልተቀበለ በግድ እንዲቀበል ማድረግ አለብን፤አልቀበልም ካለም ከተማችንን ጥሎ ይውጣ በማለት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የኦነግን ባንዲራ እስከመስቀል ደርሰዋል።ምንም እንኳን በዬትምህርት ቤቱ አብዛኛው ተማሪ ባይገኝም በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች በሚማሩበት ት/ቤት በተገኙት ግፋ ቢል  ከአሥራና  ከመቶ በማይበልጡ ተማሪዎችና የሥርዓቱ ተቀጣሪና የኦሮሙማ አቀንቃኝ በሆኑ ጥቂት መምህራን ባንዲራው ሊሰቀልና የጥላቻ ጨኸቱም ሊደመጥ ችሏል።

የከተማዋን አስተዳደር በተቆጣጠረው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የትምህርት ቢሮ ሃላፊ የሆነው ፤ከዚህ በፊት የአዲስ አበባን ሕዝብ ከርሳምና ፈርሳም ብሎ የተሳደበ ሙላቱ ተሾመ የተባለ ባለጌ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች አሰተዳደሮችና መምህራኖች የወጣውን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በደብዳቤ ትእዛዝ ሰጥቷል።ሕጻናት ተማሪዎች ሲገቡ ሲወጡ እንዲፈተሹ፣መምህራንና ተማሪዎች መዘግዬትም ሆነ መቅረት እንደማይችሉና ቢዘገዩም ሆነ ቢቀሩ አስፈላጊው ቅጣት እንደሚጣልባቸው፣ከትምህርት ጊዜ ውጭ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ እንዳይቆዩ ---ወዘተ የሚሉ አስገዳጅ ደንቦችን አውጥቶ ልኮላቸዋል።

ይህ በእንዲህ እያለ በሌላ በኩል የሥርዓቱ ተቀጣሪ ውታፍ ነቃይ ጋዜጠኞችና  ዩቱበሮች አብይ አህመድና የሚመራው መንግሥት በአዲስ አበባ ውስጥ የኦነግ ባንዲራ እንዳይሰቀልና መዝሙሩም

እንዳይዘመር ከለከለ በማለት የሃሰት ወሬ በመንዛት የሕዝቡን ትግልና ተቃውሞ ለማለዘብ ሞክረው እውነቱ በመጋለጡ ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

በዚህ አሻጥር ያልተሳካለት ተረኛው የኦነግ ቡድን እውነተኛ ገጹን እያሳዬ በመምጣቱ ይደግፉት የነበሩ የኦሮሞ ተወላጆች ሳይቀሩ ትክክል አለመሆኑን እዬገለጹና እዬተቃወሙት መሆኑን ታዝበናል።ከነዚያም ውስጥ ለእንግልትና ለእስራት የተዳረጉ ጥቂቶች አይደሉም።ሆኖም ግን የሕዝቡ ትግል ካልተጠናከረ የእነዚህ ኦሮሞዎች ተቃውሞ ቀጣይነቱ ያጠራጥራል።የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና ተቋማትም የሕዝቡን ተቃውሞ በመቀላቀል ድምጻቸውን እያሰሙ ነው።የነሱም ተቃውሞ አይተነው ጊዜ በሚል የአድር ባይነት ጉዞ ቢሆንም ቀጣይነት የሚኖረው የሕዝቡን ትግል ግለት ተከትሎ ነው። የሕዝቡ ትግል ከተዳከመ ወደነበሩበት የመንግሥት አጃቢነት ካምፕ ይመለሳሉ። ሥርዓቱ የሚመራበትን አገር አጥፊ ሰነድ ተቀብለው በሕጋዊነት ከተመዘገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ አይጠበቅም።አብዛኛዎቹ ድምጻቸውን ከማሰማት ተቆጥበዋል።የሥልጣን ቁራጭ ከተሰጠው በኋላ ሌላው ቀርቶ የመኖሩን ደብዛ ያጠፋው የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ የሚባለው በበዬነ ጴጥሮስ የሚመራው ፓርቲ አንዱ ምሳሌ ነው።ከሃምሳ በላይ የሆኑት የፖለቲካ ድርጅት  መሪዎቻቸው ላገኙት ቅንጣቢ ሥልጣንና ደመወዝ እንዲሁም የገንዘብ ድጎማ ሲሉ አገርና ሕዝብን የሚያክል ትልቅ የጋራ ሃብት አሳልፈው ሰጥተዋል።አብይን አጅበው ተንደርድረው አገር ቤት የገቡ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሕዝቡን በማደንዘዝ  የጥፋቱ ተጠያቂዎች ናቸው።አሁንም ድረስ ለፈጸሙት ስህተት ማብራሪያና ይቅርታ አልጠዬቁም። አብዛኞቹም በጎሳና የክልል ማንነት የተቋቋሙ በመሆናቸው የከባቢያቸውን ሃብት በመዝረፍና በመከፋፈል ላይ ስለተጠመዱ  ለፍትሕና ዴሞክራሲ፣ለአገር አንድነት ይቆማሉ ተብሎ አይጠበቅም። አማራውና ሌላው አገር ወዳድ በሥርዓቱ ሲበደልና የመከራ ኑሮ ሲገፉ፣ ሲጨፈጨፍና ሲፈናቀል ድምጽ ከማሰማትና ለምን ብሎ ከመጠዬቅ ይልቅ ዝምታን መርጠዋል።ይህ ዝምታቸው ግን እራሳቸውንም በኦነግ ኦሮሙማ  ለተቀጣጠለው የጭፍጨፋ ሰደድ  ጭራሮ ያደርጋቸዋል እንጂ የሚያድናቸው አይሆንም።ለዚያም ማሳያው እያንዳንዱን ክልል መውረሩና ማሶረሩ ፣ሕዝቡን ማፈናቀሉ በአፋር፣በሶማሌ፣በደቡብ የታዬው በቂ ማስረጃ ነው።ወደፊትም እያንዳንዱ ጎሳና ክልል የሚጠብቀው ካለፈው የከፋ ይሆናል።የያንዳንዱ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ሊገጥመው ከሚችለው አደጋ ለመዳን የግድ ካለው የጎሳ ሥርዓት እራሱን መነጠልና በኢትዮጵያዊነት ቆሞ የተሸከመውን የጎሰኞች ሥርዓትና ሕገ ጥፋቱን  ማሶገድ ብቻ ነው።ይህንን ሳይገነዘብ ቀርቶ ለአደጋው ሲጋለጥ ያዙኝ ልቀቁኝ ብሎ ቢጮህ ሰሚ አያገኝም።ያልጠረጠረ ተመነጠረ!

አሁን ትግሉ ከሞትና ሽረት ደረጃ ላይ ደርሷል።ተረኛው የኦሮሙማው ቡድን በገጠርም በከተማም ኢትዮጵያዊነትንና አማራውን ለማጥፋት ቆርጦ ተነስቷል። እንዲሁም ሥርዓቱን የማይቀበሉትን የኦሮሞ ተወላጆች ሳይቀሩ እያሳደደና እዬገደለ፣በእስር ቤትም እያጎረ ነው።የሌሎቹም ጎሳ ተወላጆች እንዲሁ። ከአማራው በላይ ለአማራውና ለኢትዮጵያ ሽንጡን ገትሮ የሚከራከረው የወላይታው ተወላጅ አዛውንቱ ታዲዎስ ታንቱ  ፍርድ ሳያገኝ በእስርቤት ውስጥ በዕድሜ ጫናና በህመም እዬተሰቃዬ  ይገኛል። በድፍረት ስርዓቱን ከሚቃወሙና ከሚያጋልጡትም መካከል መስከረም አበራና የባልደራስ ፓርቲ አመራሮች የኦሮሙማው ቡድን በተለይም የአብይ አህመድ የበቀል ብትር ማረፊያዎች ሆነዋል።

የዚሁ የተገንጣዬች አውራና ፊት አውራሪ የሆነው ወያኔም በመሃል አገር ከኦነግና መሰል የሽብር ቡድኖች ጋር በመተባበር የሚፈጽመውን ወንጀል ቀጥሎበታል።ከሥርዓቱ ባለቤቶች ጋር የዓላማ ልዩነት ባይኖረውም በስልጣን ቅርምት ምክንያት ገብቶ የነበረበትን አታካሮ በሰላም ድርድር ፈትቻለሁ ቢልም መሣሪያ ላለማስረከብ ምክንያት እዬደረደረ መጥቷል።ምክንያት መደርደርም ብቻ ሳይሆን በሃይል ይዞ በሃይል የተነጠቀውን የአማራውን አጽመ-እርስት የሆኑትን ቦታዎች፣ማለትም ወልቃይትና ጠገሌን፣ራያና

ቆቦን በሃይል መልሼ እነጥቃለሁ ከዛም ትግራይን እገነጥላለሁ ብሎ ለአራተኛ ጊዜ ወረራ ለማካሄድ ጦሩን እያሰባሰበና አዲስ ሃይል እያሰለጠነ መሆኑ ተሰምቷል።ማሰባሰብም ብቻ ሳይሆን ኮረምና ሰቆጣን በቅርብ እርቀት ከቦ ይዟል። ለሕዝቡ በእርዳታ ስም የሚገባው የምግብ እርዳታና የመቋቋሚያ ገንዘብ ተፋሰስ ለጦርነቱ ዝግጅት ላይ ማዋሉ በገሃድ ታይቷል።ምዕራባውያንም ከወያኔ ጋር ተጣብቀው የጡት አባትነት ግዴታቸውን በመወጣት ላይ ናቸው።እነዚሁ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ስም የሚነግዱ ወራሪዎች የኢትዮጵያን መፈራረስና የአማራውን መዳከም እንደ ዋና ግብአት አድርገው ከወሰዱ ውሎ አድሯል።ለእነሱ ኢትዮጵያን ማፈራረስ ማለት ሌላውን የአፍሪካ አገር ለማፈራረስ የሚንደረደሩበት መንገድ ጠረጋ ማለት ነው።ለዚያም ነው የአማራው እልቂትና ስቃይ የማይሰማቸው።የወያኔን ወንጀል በመሸፋፈን ይባስ ብለውም እንደ ተበደለ አድርገው ወንጀሉን ሁሉ በአማራውና በኤርትራውያን ላይ ለመደፍደፍ ይሞክራሉ።ወያኔ ለፈጸመው ወንጀልና የሰብአዊ መብት ጥሰት ይጠዬቅ ሳይሉ ጣታቸውን በአማራውና በኤርትራውያን ላይ ይቀስራሉ።

አውሮፓውያን በአገራቸው ላይ ከሰማንያ ዓመት በፊት ጀምሮ ለተፈጸመው የናዚዎች ወንጀል እስከ አሁን ድረስ ፋይሉን አልዘጉም።በዓለም ዙሪያ እያደኑ ለፍርድ ያቀርባሉ። ከሰሞኑ የናዚ ካምፕ ጸሃፊ በነበረችውና አሁን የ96 ዓመት አሮጊት በሆነችው ላይ ለቀረበባት ክስ የጀርመን ፍርድ ቤት ፍርድ ሰጥቷል።በነሱ ዘንድ የወንጀል አሮጌ የለውም።ወንጀለኛ ባጠፋው ጥፋት ይጠዬቃል፣ይቀጣል። ለኢትዮጵያና ለቀረው ያፍሪካ ሕዝብ ግን ፍትሕ ገደል ቢገባ ደንታ የላቸውም።

ኦነግ ከመሃልና ከጎን ወያኔ ከሰሜን በመመካከር የሚፈጽሙት አገር የመበታተንና አማራውን የማጥፋት ዘመቻ እስከመጨረሻው ድረስ መፍትሄ ካላገኘና ሁለቱም በሃይል ተንበርክከው ካልጠፉ በቀር አማራውና አገር ወዳዱ በሰላም ይኖራል፣የኢትዮጵያም አንድነት ይረጋገጣል ተብሎ አይታሰብም።ሁለቱ ተደራድረው የሚያመጡት የአገር ሰላምና አንድነት የለም።በአንዳንድ የዋኾች በኩል የእርቅና ሰላም ውይይት ይደረግ፣ የይቅርታ መንገድ ይከፈት ሲሉም ይደመጣል።ሰላም ሊሰፍን የሚችለው ጸረ ሰላም የሆኑ ሃይሎች ሲጠፉ መሆኑን የዘነጉት ይመስላል።እርቅም ይውረድ ሲባል እንዲሁ ገዳይና አሸባሪ በፈጸመው ወንጀል ሳይጠዬቅና ተገቢውን ቅጣት ሳያገኝ ይታለፍ ማለት እንዳልሆነ አልተረዱትም።ይህ ከሆነ ለቀጣዩ ወንጀለኛ የልብ ልብ የሚሰጥና ፍትሕን የሚጻረር አካሄድ መሆኑንና ተቀባይነት እንደሌለው ሊያውቁት ይገባል።

የዓብይ አህመድ ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናና የወያኔ ቡድን በሚስጢር የተግባቡበትን ኢትዮጵያን የማፍረስ ሴራና የነጻ አገር ግንባታቸውን እውን ለማድረግ ለድጋሚ ውይይት በኬንያ ከተማ ናይሮቢ ተገናኝተዋል።ወያኔ ሙጭጭ ያለው ሕገመንግሥቱ ይከበር በሚለው ዋና ጥያቄ ላይ ሲሆን ያም አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን ተግባራዊ የማድረግ ፍላጎት ነው።ትግራይም ተገንጥላ የኤኮኖሚና የውጭ ግንኙነት በር እንዳታጣ የወልቃይትና የጠገሌ፣የራያና ቆቦ ለም መሬቶች ወሳኝነት አላቸው።ያንን ለማድረግ የአቅም ግንባታ ለማግኘት በአብይ አህመድ መንግሥት ውስጥም ቦታ ለመያዝ የድርድሩ አንዱ ነጥብ ነው። ከአሜሪካ መሪዎችም ጋር አብይ አህመድ የተስማማበትና ለማስፈጸምም ቃል የገባበት አንዱ ነጥብ ይኸው ነው።ያንን ለማጠናከር ሲሉ ለዳግመኛ ውይይት ኬንያ ተገናኝተዋል።የሚገርመውና ለሕዝቡ ግልጽ ያልሆነለት ነገር ውይይቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በትግራይ ክልል አመራሮች የሚለው አጠራር ነው። ይህ በራሱ ትግራይን የኢትዮጵያ አካል አለመሆኗን በተዘወዋዋሪ እውቅና የመስጠት አቀራረብ ሆኖ አገኘተነዋል። ሁለቱም የሚደራደሩት ለመገንጠል በሚያስችላቸው ላይ እንጂ ኢትዮጵያን እንደ አንድ አገር በማጽናቱ ላይ አይደለም።አብይ አህመድ ለወያኔዎቹ እውቅና ሲሰጥ ወያኔዎቹም ለአብይ አህመድ እውቅና ሰጥተውታል። በናይሮቢ የተደረገው የሰሞኑ ግንኙነትም ያንን ለማጽናት ነው።

የነዚህ ሁለት ከይሲ ቡድኖች ድርድር ለሰላም የሚያበቃ ነው ብሎ መገመት ከእባብ እንቁላል እርግብ ይፈለፈላል ብሎ የመጠበቅ ያህል ጅልነት ነው።

ዘላቂ ዓላማቸውን ለማስፈጸም የሕዝቡን ተቃውሞና ትኩረት በልዩ ልዩ አጀንዳ ለማዘናጋት የአብይ አህመድ አገዛዝ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አጠናክሮ ቀጥሎበታል።

1 በወለጋና በሌሎቹ የኦሮሞ ክልል ቦታዎች የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አሸባሪ ቡድን ግድያና ጭፍጨፋውን አጠናክሮ እንዲቀጥል

2 በአዲስ አበባ የኦነግን ባንዲራና መዝሙር በተማሪው ላይ አስገድዶ የመጫን ሙከራ በመንግሥታዊ ተቋማት በኩል ማስፈጸም

3 ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት መሠረት የሆኑትን የአማራውን ማህበረሰብና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ እምነትን ማዳከም፤ለዚያም መሪና ተሰሚነት አላቸው የሚላቸውን አድኖ ማጥፋት

4 የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮው ከባድና መራር እንዲሆንበትና ለችግር እጁን ሰጥቶ ለጥ ሰጥ ብሎ እንዲገዛ ማድረግ

እነዚህን እኩይ ተግባራት ለማስፈጸም የዬክልሉ አድርባዮችና ምስለኔ የሆኑት አስተዳዳሪዎች ተባባሪ ሆነዋል።ብአዴን የተባለው በአማራው ስም የተቀመጠው ባንዳ ቡድን አንዱና ግንባር ቀደም ነው።

በሰሞኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ በአብይ አህመድ በኩል የተከፈተውን ዘመቻ በፓስተር ዮናታን በኩል በተረጨው መርዝ ለመታዘብ ችለናል።ይህንን ተከትሎ የተለያዩ የእምነት ተቋማት በጋራ በመሰረቱት መድረክ ላይ ቀርቦ ውሳኔ ከሰጡበት በኋላ መግለጫ ለመስጠት በተጠራበት ቀን በአብይ አህመድ ትእዛዝ የሙስሊምና የፕሮቴስታንት ተወካዮች እንዳይገኙ ሲደረግ በእለቱ በቦታው ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶና የኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተጠሪዎች ብቻ ተገኝተዋል።ቀድሞም የሙስሊሙን የእምነት ተቋም ከሸህ ሙፍቲ የመጅሊስ አመራር ነጥቆ በራሱ ተከታይ በሆነ ከአሩሲ ባመጣው የኦሮሙማ ሸህ መተካቱ ለዚህ ዓላማ እንዲመቸው ነበር። በዚህ ብቻም አልቆመም በመጪው ጥር ወር የሚከበረውን የጥምቀት በዓል በተመለከተም ይኸው ተረኛ የኦነግ መንግሥት ስለ በዓሉ አከባበር ግዴታ አስቀምጧል።ያም ግዴታ የወይበሷ ማርያም ታቦት ለዘመናት ሲያርፍበት በነበረው ቦታ ላይ ማረፍ እንደማይችል የሚከለክል ትዕዛዝ ነው። በዚህ ቅጥ ያጣ ድፍረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ አቅርበዋል። ይህንን የተረኞቹን ድፍረት በውስጥና በውጭ አገር ያለ ሁሉም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይና ለዴሞክራሲና ለሰላም የሚታገል የሌላው እምነት ተከታይ ሊቃወመውና ከቤተክርስቲያኗ ጎን እንዲሰለፍ ጥሪ እናደርጋለን።ይህ የዛሬው ድፍረት የተጀመረው ዛሬ ሳይሆን ቆይቷል። አብይ አህመድ ከሁለት ዓመት ተኩል በፊት በኢትዮጵያ የፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋት የ50ኛው ዓመት ሲከበር በቦታው ተገኝቶ ባሰማው ንግግር እንዲህ ብሎ ነበር “የዛሬ 50 ዓመት ሊውጠን አፉን ከፍቶ የነበረው አንበሳ በክርስቶስ ፈቃድና ሃይል ተሸንፎ አሁን ለደረስንበት ቦታ በቅተናል።ፈጣሪ የቅራቅንቦ አምላክ አይደለም” በማለት ታዳሚውን አስጨብጭቦ ነበር።አባባሉን ስንመረምረው በአንበሳ የመሰላት በጊዜው ትቃወም የነበረውን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ሲሆን ቅራቅንቦ ያለውም የእምነት የቅዳሴና ዜማ ባህላዊና እምነታዊ ምልክት የሆኑትን ታቦት፣ከበሮና ጽናጽን ነበር።ይህንን ደፍሮ የተናገረ ባለጌ ጸረ ኢትዮጵያ ግለሰብ የባሰ ድርጊት ከመፈጸም ይመለሳል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው። በታቦቱ ወይም በጽላቱ ላይ የሰፈሩት መለኮታዊ ትእዛዞች ማለትም አትስረቅ፣አትግደል፣ አትዋሽ፣አታመንዝር፣ ሌላውን(ወንድምህን) እንደራስህ ውደድ--ወዘተ የሚሉትን ቢቀበልና ቢያከብር ኖሮ ቅራቅንቦ ብሎ

ባልተሳደበ ነበር።ለእሱ ክብርና ዋጋ የሚሰጠው ነገር ቢኖር ሰውን ከሰው፣ጎሳን ከጎሳ፣ጾታን ከጾታ የሚያባላውን፣አገር የሚያፈርሰውን ደንብና መመሪያ የያዘ አገር አጥፊ ሥርዓትና መመሪያ መሸከም ነው።ይህንን ባለጌ ነው ፈጣሪ የመረጠውና የቀባው፣በሽዎች ዓመት አንድ ጊዜ ብቅ የሚል ደግና አስተዋይ መሪ፣እያሉ የሚያሞካሹት።ከጎሳ ማንነት ጋር ያልተሳሰረው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ግን ለእውነትና ለፈጣሪ ቃል በመገዛት የኦሮሙማውን ሥርዓትና ወንጀል በማውገዝ ላይ ናቸው። እስከአሁንም ድረስ ያላወገዙ ካሉ እንዲያወግዙ ጥሪያችን ነው።

የሕዝቡ ብሶት በያቅጣጫው በመታዬት ላይ ነው።የአዬር መንገድ ሠራተኞችም በአስተዳደሩ ላይ ተነስተዋል።የደመወዝ ጭማሪና የመብት መደፈርን የተቃውሞ ማእከላቸው አድርገዋል።ለጥያቄያቸው ተገቢ መልስ ካልተሰጠ የሥራ ማቆም አድማ እንደሚመቱ አስጠንቅቀዋል።አገዛዙ ካላወቀበትና በለመደው የጉልበት መንገድ እፈታለሁ ካለ እርሟን አንድ ጥርስ ቢኖራት እሱንም በዘነዘና ተወቀረችው ወይም አንድ ዓይን ቢኖራት በስንጥር አፈረጠችው ይሆናል።የተነሳበትን የሠራተኛውን ጥያቄና የአድማ ማስጠንቀቂያ ለማኮላሸትና ለመሸፋፈን  በውታፍ ነቃይ ጋዜጠኞቹ በኩል ስለ አዬር መንገዱ እድገት፣ ስላመጣው  ትርፍ፣ለወደፊቱ ስላለው እቅድ በተደጋጋሚ ሲያስነግር ሰንብቷል።በተዘዋዋሪ ማስተላለፍ የፈለገው ይህንን ጉዞ ለማደናቀፍ የሚሞክር ቢኖር ጸረ ሰላምና ጸረ እድገት የሆነ ብቻ ነው የሚለው ይሆናል።ስለሆነም የሠራተኛው ጥያቄ በውድም በግድም ይደፈጠጣል ማለት ነው።በሌላም መንገድ አዬር መንገዱን ባጥለቀለቀው የኦሮሙማ ካድሬ በኩል መከፋፈል እንዲነሳና የሌላው ጎሳ ተወላጅ በሆኑት ላይ እርምጃ ለመውሰድ የታቀደ ሊኖር እንደሚችል አዝማሚያው ያመላክታል።

አንዱና  ጠንካራው ያገሪቱ የገቢ ምንጭ  የሆነውን አዬር መንገድ ለመሸጥ ብዙ ሴራ እንዳለ የሚታወቅ ነው።ስለአዬር መንገዱ እድገት ማውራቱ ሽያጩን ለማፋጠን  እንደማስታወቂያ  ሳይጠቀምበት የቀረ አይመስለንም።ሌላውም ዘዴ የሠራተኛው ጥያቄ ሳይመለስ የሚፈጠረውን  ቀውስ  የሽያጩ ምክንያት ለማድረግ ይጠቀምበታል የሚል ጥርጣሬ አድሮብናል።

የሕዝቡን ትግልና ተቃውሞ ሌላ አቅጣጫ ለማስያዝ የማይሞከር ነገር የለም።ሕዝብ በርሃብ  በሰሜን በደቡብና በመሃል አገር በአዲስ አበባ ሳይቀር እንደቅጠል እዬረገፈ አብይ አህመድ የሥርዓቱ ደጋፊዎችና የኦሮሙማው አካል የሆኑ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ የተገዛ የእርሻ መሣሪያ ታድለው የሰፊ እርሻ ባለቤት ሆነው ያመረቱትን በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ዘርፍ በኩል ለጎረቤት አገር አውጥተው እንዲሸጡና ገንዘቡን ለክልሉና ለራሳቸው እንዲቀራመቱ ለማድረግ  ኢትዮጵያ በቅርቡ ስንዴ አምርታ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ከሚያስችል አቅም ላይ ነች በማለት ተመጻድቋል።የራሷ እያረረባት የሌላ ታማስላለች እንደሚሉት መሆኑ ነው።

ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው የችግሩ መንስኤ የጎሳ ፖለቲካውና የሚመራበት ሕገ ጥፋቱ ነው። የኦነግ ኦሕዴድም ሆነ የወያኔ ፍላጎት ኢትዮጵያን አፈራርሶ በፍራሿ ላይ ዬዬራሳቸውን ክልል ብለው የያዙትን መሬት አገራዊ ቁመና እንዲኖረው ማድረግ ነው።ያም ቢሆን በከፊል ብቻ  ሳይሆን ከሞላ ጎደል የተሳካላቸው ይመስላል።በመጀመሪያ ክልልና የዬክልሉን ባንዲራ መቀበሉ የዚያ እውቅና መጀመሪያ ነው።የኦነግን ባንዲራና መዝሙር የኦሮሞ ሕዝብ አድርጎ መቀበሉ  የወያኔንና የሌሎቹንም ክልልና ባንዲራ መቀበሉ ለጎሳ ሥርዓቱ እውቅና መስጠት ነው።እንደ  አንድ ኢትዮጵያዊነት፣እንደ አንድ አገር ዜግነት የሚያስብ ዜጋ  አንድ አገር፣አንድ ሰንደቅ ዓላማ ና አንድ ሕዝብ ይላል እንጂ የተለያዬ ማንነትና የተዘበራረቀ ባንዲራ አይሸከምም።

በፖለቲካም ሆነ በሌላው መስክ  የሚፈልጉትን ለማግኘት ከሚፈልጉት በላይ መጠዬቅ የተለመደ ስልት ነው።ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናም ሆነ ወያኔ የማይገባቸውን ለማግኘት ብዙ ሙከራ አድርገዋል ብዙ

ጥያቄም አቅርበዋል፤ሃይልንም ተጠቅመዋል።ይህ ማለት ግን እውነት ከነሱ ጋር አለችና የሚፈልጉትን ያግኙ ብሎ ለመወሰን የሚያበቃ ፍትሃዊ መንገድ አይደለም።

የሥርዓቱን ምንነት ካጋለጡት የሰሞኑ ጉዶች ውስጥ አብይ አህመድ በሚስቱና በራሱ በኩል የተፈጸመውን የሌብነትና የሙስና ሰንሰለት ሊያጋልጥ የሚችል መረጃ ሲወጣበት ያደረገው መንደፋደፍ አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአማራው ስም በወያኔ ተደራጅቶ ላለፉት 32 ዓመታት የሥርዓቱ አገልጋይ ሆኖ አማራውን የሚያጠቃውና የሚያስጠቃው ብአዴን የተባለው ቡድን መሪ የሆነው አገኘሁ ተሻገር የተባለ በአማራው ደምና በአልኮል የሚንቀሳቀስ ባንዳ ለቀረበለት የሕዝብ ጭንቀታዊ ጥሪ የሰጠው የሚዘገንን ምላሽና አስተያዬት ነው።

አብይ አህመድ ሌብነቱን ለመሸፋፈን ሲል "ሌብነት አለ፣ብዙ ተሰርቋል አይካድም ግን ሌባን ማሳደዱ ችግር ላይ ጥሎናል፤ መፍትሔ ስለማይሆን ሌቦች የሰረቃችሁትን ገንዘብ በልማት ዘርፍ ላይ አውሉትና ኢንቬስተር ሁኑ" ሲል ስርቆትን ሕጋዊ እውቅና ሰጥቷል።በሱ ና በሚስቱ እንዲሁም በሌሎቹ ወደውጭ የወጣው ገንዘብ እንደማይመለስ እዬታወቀ፣ያጋለጡትን እያሳደደና እያሰረ ሌቦቹን ኑና አብረን እንስራ ማለቱ ለሕዝቡ ያለውን ንቀት ማሳያ ነው።መጀመሪያ እስኪ እራሱ ከውጭ አገር አገኘሁ ያለውን በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ስንትና በምን ላይ እንደዋለ በገለልተኛ የሂሳብ ኦዲተሮች የተረጋገጠ ማብራሪያ እንዲቀርብ ፈቃደኛ ይሁን? በዚህም አልቆመም ሰሞኑን በደቡብ ክልል በሚስቱ በኩል የተዘረፈበትን አንድ ፕሮጀክት ለመመረቅ በተገኘበት አጋጣሚ በአማራው ትግል ላይ የሰጠው አስተያዬት ያለውን ጥላቻና ሊወስድ ያሰበውን እርምጃ አመላካች ነው።የአማራውን ፍትሓዊ ትግል ከፍትሕ አልባው ከኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የጭፍጨፋ ተግባር ጋር በማያያዝና በማመሳሰል "አገር ለማፍረስና ያገሪቱን ቅርጽና ካርታ ሊለውጥ የሚችል የሁለት ጸረ አንድነት ሃይሎች የሆኑ የኦነግ ሸኔና የአማራ ሸኔ እንቅስቃሴ ነው" በማለት አዲስ ስያሜ ይዞ ብቅ ብሏል።አጥፊና ጠፊን፣በዳይና ተበዳይን፣ ጨፍጫፊና ተጨፍጫፊን በአንድ ተራ ያስቀመጠው አብይ አህመድ ለኦነግ ሸኔ የሚያቀርበውን የመሳሪያ፣የገንዘብና የመረጃ አቅርቦት ለመሸፋፈን ያደረገው የማምለጫ ዘዴ እንደሆነ ጥርጥር የለውም።

ጉድና ጅራት ከኋላነው እንደሚባለው ሌላው ጉድ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሊቀመንበር በሆነው በዶር ዳንኤል በቀለ በኩል የተሰጠው ማብራሪያ ነው።ይህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እዬተከታተለ በማጋለጥ ፍትሕ እንዲሰፍን ይረዳል ተብሎ የሚጠበቀው ተቋም ተጠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት ዘር ተኮር የሆነ የማጥፋት ዘመቻና ጭፍጨፋ(ጄኖሳይድ)አልተፈጸመም በማለት ሽምጥጥ አድርጎ በመካድ የአብይን አገዛዝና የኦሮሙማና የወያኔን ወንጀለኛ ስብስብ ለማዳን ያደረገው ያድርባይነት እርምጃ ከመሆን ያለፈ እውነትንና የዓለም አቀፍን ትንታኔ የተከተለ ነው አንልም።ሌሎቹ የተቋሙ አባላት በዶር ዳንኤል ትንታኔ ላይ ያላቸውን አንድነት ወይም ተቃውሞ እንዲገልጹ እያሳሰብን የማይገልጹ ከሆነና ተመሳሳይም አቋም ካላቸው በወንጀል ተባባሪነት እንደሚጠዬቁ ልናሳስባቸው እንወዳለን።የሰው ልጅ በሆድ ውስጥ የተጸነሰ፣ገና የሳምንት ዕድሜ ያለው ሕጻን፣ወጣት ፣ሴት፣ወንድ፣ አሮጊትና ሽማግሌ በጎሳ ምንነቱ፣በሚናገረው ቋንቋና በሚከተለው እምነት ምክንያት ተለይቶ የሚጨፈጨፍ ከሆነ ከዘር ማጥፋት ወይም ጀኖሳይድ ሌላ ከቶ ምን አይነት ስያሜ ይሰጠዋል?

ሌላው የሚዘገንነው በወለጋ የሚጨፈጨፉት የአማራ ተወላጆች በአማራ ስም ለተቀመጠው ብአዴን ለተባለው ባንዳ ድርጅት መሪ ለሆነው አገኘሁ ተሻገር ለሚባል ጉደኛ ስልክ ደውለው ድረሱልን ብለው ሲጠይቁት "በሌላ ክልል ውስጥ የገባችሁት እራሳችሁ ናችሁ፣ባመጣችሁት ጣጣ እራሳችሁ ተወጡት፣እኛ ምንም ልናደርግላችሁ አንችልም፣የክልሉ መንግሥት እንዳደረገ ያድርጋችሁ"

በማለት  ጥሪውን  ሳይቀበል መቅረቱ ብቻ ሳይሆን በግፍ የሚጨፈጨፉትን የአማራ ተወላጆች በአገራቸው መሬት ሳይሆን በሰው አገር የገቡ ወንጀለኛና ጥፋተኛ አድርጓቸዋል።ሃላፊነት የሚሰማው ቢሆንማ ኖሮ በስሙ ሥልጣን ላይ የተቀመጥኩት ሕዝብ ግፍና በደል ለምን ይደርስበታል ብሎ መነሳት የሚጠበቅበት ነበር።በታደሉት አገሮች አንድ ዜጋቸው በውጭ አገር ወንጀል ሰርቶና ሕግ ጥሶ ሲታሰርባቸው ተከራክረው የሚያስፈቱትን ከዚህ አይነቱ ከንቱ ሰው ድርጊትና አባባል ጋር ሲያስተያዩት ያለንበትን ሥርዓትና ያሉትን መሪዎች ጭካኔ የሚያጋልጥ ምሳሌ ነው።

ደግመን ደጋግመን እንደምናሳሰበው በዩጊዜውና በዩቦታው የሚካሄዱት የአገር ወዳዶች ትግል ውጤታማ እንዲሆኑ በአንድ ከሁሉም  የተውጣጣ አገር አቀፋዊ አስተባባሪ አካል ይመራ እንላለን።ያ ካልሆነ የቁራ ጩኸት ከመሆኑም በላይ በተናጠል ከንቱ መስዋእት መክፈል ይሆናል።

ሌላው በፋኖ ስም ጎፈሬ አበጥሮ ፎቶ ግራፍ እዬተነሳና ከብአዴን ጋር እዬታከከ ለቦታና ለሽልማት እጁን የሚዘረጋ፣ለብአዴን እውቅና የሚሰጥና የኢሕአዴግ- ብልጽግናን ባንዲራ የሚያውለበልብ የከተማ አውደልዳይ ከሚያደርገው ተግባር እንዲቆጠብ ማሳሰብ እንወዳለን።እውነተኛ ፋኖነት በሽምቅ ውጊያ የጠላትን ሃይል ለመስበር የተዘጋጀ ሆኖ መገኘት ሲሆን ትጥቅና ስንቁንም ከጠላት ካዝናና መጋዘዘን(ግምጃ ቤት )የሚያገኝ  ነው።ሕዝቡን የሚያራቁት፣በዶላርና በኤሮ የሚነግድ  ፋኖ በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።ይህ ማለት ግን በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለእውነተኞቹ ፋኖዎች ትግል እርዳታ አያድርግ ማለታችን አይደለም።ለተቸገሩት ወገኖቻችንና የነሱን መብት ለማስከበር፣ያገራችንንም  አንድነትና ልዑላዊነት ለማረጋገጥ፣ያለውን የጎሰኞች ሥርዓት ለማሶገድ የሚደረገውን ሕዝባዊ ትግል መርዳት የሁሉም አገር ወዳድ ግዴታ ነው።

ለወሳኙ ትግል እንሰለፍ!ሁሉም የሚችለውን ያበርክት!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!